# በባህልና ቱሪዝም ሚኒስቴር

# የቅርስ ጥናትና ጥበቃ ባለሥልጣን

# የቅርስ ውሰት መመሪያ

## ቁጥር 766/2013

ሐምሌ 2005 ዓ.ም.

አዲስ አበባ

## መግቢያ

የስብስብ ማእከሎች የሌላቸውን የቅርስ አይነቶች ከሌሎች አቻ  ማእከሎች ወይም ሙዚየሞች ጋር በመዋዋስ ፣በመደጋገፍ እና የወዳጅነት ትስስርን በመፍጠር ለሚፈልጉት አላማ ማለትም ለጥናትና ምርምር፤ ለዐውደ ርዕይ፤ ለትምህርትና ለመሳሰሉት መጠቀም አስፈላጊ ሆኖ በመገኘቱ፤

የስብስብ ማእከሎቹ ለጐብኚዎች ከሚሰጡት አገልግሎት በተጨማሪ በተለያየ አገር አቀፋዊና ዓለም አቀፋዊ ግንኙነታቸው ወቅት ቅርስን በጊዜያዊነት ሊዋሱና ሊያውሱ እንደሚችሉ የታወቀ በመሆኑ፤

በአቻ ተቋማት መካከል የቅርስ ውሠት ሂደትን በተቀላጠፈ ሁኔታ በሕግ ማዕቀፍ ላይ ተመስርቶ ለማካሄድ የሚያስችል አሰራር መፍጠር አስፈላጊ ሆኖ በመገኘቱ፣

በአዋጅ ቁጥር 209/1992 አንቀፅ 46 ንዑስ አንቀፅ 2 መሠረት ይህ መመሪያ ወጥቷል፡፡

<u>ክፍል አንድ</u>

## 1. አውጭው ባለሥልጣን

የባሕልና ቱሪዝም ሚኒስቴር በቅርስ ጥናትና አጠባበቅ አዋጅ ቁጥር 209/1992 አንቀጽ 46 ንዑስ አንቀፅ 2 በተሰጠው ሥልጣን መሠረት ይህንን መመሪያ አውጥቷል፡፡

## 2. አጭር ርዕስ

ይህ መመሪያ የቅርስ ውሰት መመሪያ ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

## 3. ትርጓሜ

የቃሉ አገባብ ሌላ ትርጓሜ ካልተሰጠው በስተቀር በአዋጅ ቁጥር 209/1992 አንቀፅ 3 የተሰጠው ትርጉም ለዚህ መመሪያም ያገለግላል፡፡ በተጨማሪም፡-

1. **ውሰት፡-**
   ለአጭር ወይም ለረጅም ጊዜ የተቋሙን ወይም የሀገርን ጥቅም በማገናዘብ ቅርስን ማዋስ ወይም በጊዜያዊነት መስጠት ማለት ነው፡፡

2. **ቅሪተ አካል፡-**
   በአሰሳ ወይም በቁፋሮ የተገኘ የሰው፤የእንስሳ ወይም የዕፅዋት ቅሪት ነው፡፡

3. **አስተሻሸግ፡-**
   ለማጓጓዝ አመቺ በሆነና ቅርሶችን በማይጐዳ መንገድ አንክብካቤ ለማድረግ  በሚያስችል መልኩ የማሸግ ሂደት ነው፡፡

4. **የመድን ዋስትና፡-**
   ከስብስብ ውስጥ ለሚወጣ ቅርስ  ተመን ወጥቶለት ለሚደርስበት ማንኛውም  ጉዳት  በካሣ  መልክ  የሚሰጥ የቅርሱ ዋስትና ማለት ነው፡፡

5. **ትራንስፖርት፡-**
   በውሰት የተሰጠውን ቅርስ ለማጓጓዝ የምንጠቀምበት የመጓጓዣ አይነት ነው፡፡

6. **የቅርስ ደህንነት ጥበቃ፡-**
   በውሰት የተሰጠውን ቅርስ በቆይታው ወቅት ሊደርግለት የሚገባ ጥንቃቄ ወይም ጥበቃ ነው፡፡

7. **የውሰት ሰጭ አካል፡-**
   በውሰት የሚተላለፈው ቅርስ ባለይዞታ ወይም ሕጋዊ ተወካይ ማለት ነው፡፡

8. **የውሰት ተቀባይ፡-**

ቅርሱን በውሰት የሚወስደው /የሚቀበለው/አካል ነው፡፡

9. **የክትትል ቡድን፡-**

ቅርሱ በውሰት ከተሰጠበት ጊዜ ጀምሮ በቆይታው ወቅት እስከ መመለሻው ድረስ ያለበትን ሁኔታ የሚከታተል በውሰት ሰጪው አካል የሚቋቋም የቴክኒክ ቡድን ነው፡፡

10. **ፈቃጅ አካል፡-**

ቅርሶች በውሰት እንዲተላለፉ ፈቃድ የሚሰጥ የቅርስ ባለይዞታ ወይም የባለሥልጣኑ ዋና ዳይሬክተር ወይም በአዋጅ ቁጥር 209/1992 አንቀፅ 27 መሠረት ሥልጣን የተሠጠው የመንግሥት አካል ነው፡፡

## <u>ክፍል ሁለት</u>

### 4. በውሰት ስለሚወጡ ቅርሶች

1. ቅርሶች ከቦታ ቦታ የሚዘዋወሩት በባለሥልጣኑ ወይም በሌሎች ባለይዞታዎች ዘንድ የማይገኙ ቴክኖሎጂዎችን በመጠቀም በምርምር ተቋማት ወይም በግለሰብ ተመራማሪዎች ለሚደረግ ጥናትና ምርምር ወይም ለትምህርት ወይም ለዓውደ ርዕይ ወይም ለጥበቃና ለእንክብካቤ ስራ ብቻ ይሆናል፡፡

2. ቅርሶች በውሰት መልክ ሲፈቀዱ ወይም ሲመረጡ በተቻለ መጠን ከስብስቦች ውስጥ ቢዋሱ ሊበላሹ የማይችሉና በአይነታቸው አንድ ብቻ ያልሆኑ መሆን አለባቸው፡፡ ነገር ግን አዋጁን መሰረት አድርጎ ለጥናትና ምርምር በውሰት የሚወጡ ቅርሶች አይነታቸው አንድ ብቻ ቢሆንም ሊፈቀድ ይችላል፡፡

3 በውሰት መልክ የሚሄዱ ቅርሶችን በምንም መልኩ ለሦስተኛ ወገን አሳልፎ መስጠት ለንግድ አላማ ማዋል አይቻልም፡፡

4. በአንድ ተቋም ውስጥ የሚደረግ የእርስ በእርስ ቅርስ ውሰት በሚመለከተው የስብስብ ክፍል ፈቃድ ተፈፃሚ ይሆናል፡፡

5. ቅርሶች ለሀገር ውስጥ የሚወጡት በተዋሹ በሚቀርብ ጥያቄ በሚመለከተው ሃላፊ ወይም ባለስልጣን በሚሰጥ የፅሁፍ ፈቃድ መሠረት ይሆናል፡፡

6. ቅርሶች ከሀገር ውጭ በውሠት የሚወጡት በአዋጅ ቁጥር 209/1992 አንቀፅ 27 በተደነገገው መሰረት ይሆናል ፡፡

7. ሀገር ውስጥም ሆነ ወደ ውጭ ቅርሶች በውሰት ሲወጡ አጠቃላይ ይዞታቸውና መረጃቸው በሠነድ ይዘጋጃል፡፡

ቅጅውም በውሰት ሰጭውና ተቀባዩ እንዲቀመጥ ይደረጋል፡፡

8. በውሰት የወጡ ቅርሶችን ከቦታ ቦታ ለማዘዋወር አስፈላጊ ሲሆን የአዋሹን አካል በማሳወቅና በማስፈቀድ ብቻ ይሆናል፡፡

9. በውሰት የሚሄዱ ቅርሶች ክፍያ የሚኖራቸው ከሆነ በባለሙያዎች ተጠንቶ በሚወሰነው መሠረት ይከናወናል፡፡

10. ቅርሶች ለውሰት የሚሰጡት ከ3 አመት ላልበለጠ ጊዜ ይሆናል፡፡ሆኖም እንደአስፈላጊነቱ እስከ ሁለት አመት ለሚሆን ጊዜ በሁለቱ ወገኖች ስምምነት ውሉ ሊታደስ ይችላል፡፡ በዚህም ወቅት ዋስትናው አብሮ ሊታደስ ይገባል፡፡

11. የዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ 10 ድንጋጌ እንደተጠበቀ ሆኖ በአሳማኝ ምክንያት ለጥናትና ምርምር በውሰት የሚወጡ ቅርሶች የጊዜ ቆይታ በባለሙያዎች ታይቶ የሚወሰን ይሆናል፡፡

## 5. የሚዋሱ ቅርሶችን ለመወሰን የሚመሰረት አጥኚ ቡድንን በተመለከተ

ቅርሶችን ለውሰት ከሚቀርቡበት ከመረጣው ጀምሮ አጠቃላይ ሁኔታዎችን አጥንቶ እስከ ማቅረብ ተግባር ያለውና ከሚመለከታቸው አካላት ማለትም ቅርሱ ከሚዋስበት ስብስብ ክፍል ሃላፊ፣ የሚመለከተው ባለሙያ፤ የቅርስ ዶክመንቴሽን ባለሙያ እና የቅርስ ቁጥጥርና ክትትል ባለሙያን ያካተተ ቡድን ተጠሪነቱ ለባለሥልጣኑ የበላይ ሃላፊ ሆኖ ይመሠረታል፡፡

## 6. የቡድኑ ኃላፊነትና ተግባር

1. በበላይ ኃላፊው ሲታዘዝ ለውሰት የሚሄዱትን ቅርሶች ያጠናል፣ይመርጣል፣
2. አጠቃላይ ሁኔታዎችን በአንቀፅ 4 በተገለፀው መልኩ ያከናውናል፣
3. በውሰት የሄዱ ቅርሶችን በተሰጠው የጊዜ ገደብ ውስጥ የሚመለሱበትን ሁኔታ ክትትል ያደርጋል፡፡

## 7. በውሰት የሚወጡ ቅርሶች ስለሚገባላቸው የመድን ዋስትና

1. በቅርሶች አይነትና ደረጃ ተመስርቶ የተለያየ የመድን ዋስትና(የኢንሹራንስ ተመን) እንዲወጣላቸው ይደረጋል፡፡
2. የመድን ዋስትና ጉዳዮችን ለማስፈጸም ተዋሹ ሙሉ ወጪውን በራሱ ይሸፍናል፡፡
3. ቅርሶች ላይ የጉዳት ወይም የመጥፋት አደጋ ቢፈጠር በተደረገው ስምምነት መሠረት ዋስትናው (የኢንሹራንስ ክፍያው) እንዲከፈል ይደረጋል፡፡
4. የበላይ ኃላፊው ክፍያው(ካሳው) ከሚመለከተው የመድን ዋስትና ድርጅት በተፈረመው ውል መሠረት መፈፀሙን ይከታተላል፡፡

## 8. በውሰት ዘመን ለሚፈጠር ቅሬታ አቀራረብና አካሄድ

1. በውሰት በወጡ ቅርሶች አያያዝ ላይ ችግር እንዳለ ከታወቀ ወይም ጥቆማ ከቀረበ ቅርሱን የሚያውሰው ወገን ጉዳዩን የሚያጠና የባለሙያዎች ቡድን ይልካል፣
2. ሁኔታውን እንዲያጠና የተላከው አካል ዝርዝር ጉዳዮችን በመመልከት አጠቃላይ ሪፖርት ለበላይ ኃላፊው ያቀርባል፡፡
3. አጥኚው አካል ወደ ውሰት ስፍራው ሲንቀሳቀስና የተጠቀሰው ችግር የተፈጠረ ከሆነ አጠቃላይ ወጭው በተዋሰው አካል የሚሸፈን ይሆናል፡፡ ይህ ባይሆን ግን በአዋሰው አካል እንዲሸፈን ይደረጋል፡፡ ይህም በስምምነት ውሉ ላይ የሚካተት ይሆናል፤

**9. በውሰት ስለሚሄዱ ቅርሶች አስተሻሸግን በተመለከተ**

ቅርሶች ከቦታ ወደ ቦታ በውሰት በሚጓጓዙበት ወቅት ከፍተኛ ጥንቃቄ ይደረግላቸዋል፡፡ በመሆኑም

የሚከተሉትን ሁኔታዎች ማሟላት አለባቸው፡-

1. የአስተሻሸጉ ሁኔታ ለቅርሶቹ ደህንነት አመቺ የሆነ፣
2. በማሸጉ ሂደት ቅርሱ ከሚወጣበት ስብስብ ክፍል የሚሰሩ ባለሙያዎች ቅርብ ክትትልና ሙያዊ ድጋፍ ማድረግ አለባቸው፡፡

**10. ለዓውደ ርዕይ በውሠት የሚወጡ የቅርሶች አያያዝ**

1. ቅሪተ አካል፣ አልባሳት፣ ልዩ ልዩ ቁሳቁስና መሣሪያዎች፣የሥነ ጥበብ ውጤቶች ለፀሀይ፣ ለዝናብ፣ ለአቧራ በማይጋለጡበት ቦታ ወይም በማሳያ ሳጥን (Showcase) መቀመጥ ይኖርባቸዋል፣
2. ጎብኝዎች በጉብኝት ወቅት ቅርሶቹን በእጃቸው እንዳይነኳቸው በማድረግና ለጎብኝዎች አመቺ በሆነ ሁኔታ ተቀምጠው መታየት ይኖርባቸዋል፡፡
3. ልዩ ጥንቃቄ የሚያስፈልጋቸውና በፎቶ ማንሻ ፍላሽ/ሙብራት/ የሚጎዱ ከሆነ በስምምነት ላይ ተገልጾ መተግበር ይኖርበታል፣

**11. የቅርሶች በውሰት የማቆያ ጊዜ ውልን ስለማቋረጥ**

1. ቅርሶች በውሰት ሲወጡ የቆይታ ወቅታቸው በአንቀፅ 4 በንዑስ አንቀፅ 10 በተጠቀሰው መሠረት ሆኖ ተዋሹ አካል የውሰት ጊዜውን ጠብቆ ካልመለሰ አዋሹ ውሉን ያቋርጣል፤ግደታውን እንዲወጣ ከተደረገ በኋላ በቀጣይ ጊዜ የወሰት ጥያቄ ቢያቀርብ አይስተናገደም፡፡
2. በውሰት የሄዱ ቅርሶችን በውሉ የተቀመጠው የጊዜው ገደብ ሳይጠናቀቅ አዋሹ አካል እንዲመለስለት መጠየቅ አይችልም፡፡
3. የዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ 2 ድንጋጌ ቢኖርም ሰጭው አካል ለቅርሱ ደህንነት አስጊ አያያዝ መኖሩንና በመበላሸት ላይ መሆኑን ሲያምንበትና ተዋሹም ይህን ሲያረጋግጥ ቅርሱን ሊያስመልስ ይችላል፡፡ለዚህም በውሰት ጊዜው የተገባው ዋስትና እንዲከፈል ይደረጋል፡፡

**12.የባለሙያ ክትትል**

1. ለቅርሶች ደህንነት ከውሰት በኋላ ተከታታይ ክትትል ለማድረግ እንዲያስችል ሁለቱ ወገኖች በውሰት ውሉ በተስማሙበት መልኩ የባለሙያ ጉብኝት ይካሄዳል፡፡
2. ቴክኒካዊ የባለሙያዎች ጉብኝት በሚያስፈልግበት ወቅትና ቅርሶቹ በቆይታቸው ወቅት ለሚደረጉ ጉዞዎች የቆይታ ወጭ በተዋሹ የሚሸፈን ይሆናል፡፡

## <u>ክፍል ሶስት</u>

**13. የመተባበር ግዴታ**

ማንኛውም ሰው ይህንን መመሪያ ስራ ላይ ለማዋል የመተባበር ግዴታ አለበት፡፡

**14. ቅጣት**

ይህንን መመሪያ የሚተላለፍ ማንኛውም ሰው አግባብ ባለው ሕግ ይቀጣል፡፡

**15. መመሪያውን ስለማሻሻል**

ይህ መመሪያ አስፈላጊ በሆነ ጊዜ የሚመለከተው ስልጣን ያለው አካል ሊያሻሽለው መብቱ የተጠበቀ ነው፡፡

**16. መመሪያው የሚፀናበት ጊዜ**

ይህ መመሪያ ከ ------------ ቀን 2005 ዓ.ም ጀምሮ የፀና ይሆናል፡፡

**አሚን አብዱልቃድር**

**የባሕልና ቱሪዝም ሚኒስትር**

**-----------ቀን/2005 ዓ.ም**

**<u>አዲስ አበባ፤</u>**